ቦርድ ኮሚሽነሮች የምርጫ አስተዳደር ከተማ የCambridge

689 Massachusetts Avenue፣ STE 1፣ Cambridge፣ MA 02139-3302
ስልክ፦ 617-349-4361 • ፋክስ፦ 617-349-4366 • ኢሜይል፦ elections@cambridgema.gov

**ኮሚሽነሮች፦**
Ethridge A. King, Jr.
Larry W. Ward Charles J. Marquardt
Sara I. Rivera

**የምርጫዎች ዳይሬክተር፦**
Tanya L. Ford

**ረዳት ዳይሬክተር፦**
Lesley Waxman

የCambridge ነዋሪ
ደንበኛ፣ MA

በቅድሚያ የተሰተረ
ለመላኪያ የተከፈለበት
መደበኛ የUS ፖስታ
CAMBRIDGE MA
የፈቃድ ቁጥር 58215

# 2026 ዓ.ም አስቀድሞ ድምጽ የመስጫ መመሪያ

CITY OF CAMBRIDGE

**የመጀመሪያ ዙር የስቴት ምርጫ**

**ሴፕቴምበር 1 ቀን 2026 ዓ.ም**

## እ.ኤ.አ ለሴፕቴምበር 1 ቀን 2026 ዓ.ም የመጀመሪያ ዙር የElection Commission የስቴት ምርጫዎች የ24-ሰዓት ይፋዊ ድምጽ መስጫ ሳጥን መገኛዎች

### ዋና የድምጽ መስጫ ሳጥን መገኛ

የሚከተለው ቦታ እስከ ማክሰኞ፣ ሴፕቴምበር 1 ቀን 2026 ዓ.ም 8 ፒ.ኤም የምርጫ ቀን ድረስ ክፍት ይሆናል።

Election Commission
689 Massachusetts Avenue
በፊት ለፊት መግቢያው የግራ ጎን

**ይህ የድምጽ መስጫ ሳጥን ቦታ እ.ኤ.አ ሴፕቴምበር 1 ቀን 2026 ዓ.ም በሚውለው የምርጫ ቀን ላይ ክፍት የሚሆነው ብቸኛው ቦታ ነው።**

### ድምጽ መስጫ ሳጥን የሚገኝባቸው ሌሎች ቦታዎች

የድምጽ መስጫ ወረቀቶች በፖስታ ከተላኩ በኋላ የሚከተሉት ቦታዎች ክፍት የሚሆኑ ሲሆን፣ ሰኞ፣ ኦገስት 31 ቀን 2026 ዓ.ም 8 ፒ.ኤም ላይ ይዘጋሉ። **ድምጽ መስጫ ሳጥን የሚገኝባቸው ሌሎች ቦታዎች የምርጫ ቀን በሚውልበት እ.ኤ.አ ሴፕቴምበር 1 ቀን 2026 ዓ.ም ላይ ክፍት አይሆኑም።**

እባክዎ **የመረጡበት ድምጽ መስጫ ወረቀት የጁራት ፖስታው** (ቢጫ ፖስታ) ውስጥ የታሸገ መሆኑን እና ፖስታውን ድምጽ መስጫ ሳጥን ውስጥ ከማስገባትዎ በፊት የጁራት ፖስታው ላይ ያለው ማረጋገጫ **የተፈረመበት መሆኑን ያረጋግጡ።**

City Hall
795 Massachusetts Avenue
ከኋለኛው መግቢያ በር አቅራቢያ

Morse **ትምህርት ቤት**
40 Granite Street
ከፊት ለፊት መግቢያ በሩ አቅራቢያ

Cambridge Police Headquarters
(**የ**Cambridge **ፖሊስ ዋና መሥሪያ ቤት**)
125 6th Street
ከህንፃው ፊት ለፊት አቅራቢያ


Maria L. Baldwin **ትምህርት ቤት**
85 Oxford Street
በOxford St. መግቢያ በቀኝ ጎን በኩል

O'Neill **ቤት-መጻሕፍት**
70 Rindge Avenue
ከመግቢያው ደረጃዎች አጠገብ

### ባለብዙ ቋንቋ አጋዥ ግብዓቶች

বাংলা
አማርኛ
عربى
Español
中文
Português
Kreyòl
English

## አስቀድመው ድምጽ ይስጡ! በፖስታ ድምጽ ይስጡ!



የCambridge Election Commission (የCambridge ምርጫ ኮሚሽን) እርስዎ በሚመችዎ መርሃ ግብር መሠረት ለመምረጥ ቀላል እና አመቺ እንዲሆንልዎ እያመቻቸ ይገኛል። በፖስታ ወይም በአካል አስቀድመው ድምጽ ይስጡ!

### በአካል በመቅረብ አስቀድሞ ድምጽ መስጠት የሚቻልበት ጊዜ

ከኦገስት 22 - ኦገስት 28 ቀን

**ጊዜያትን እና ቦታዎችን ለማየት ውስጥ ይመልከቱ!**

## የመራጭ ምዝገባ ሁኔታዎን ያረጋግጡ

**www.RegisterToVoteMA.com**
ወይም ለElection Commission office በ617-349-4361 ይደውሉ።

*የመመዝገቢያ ወይም ስምዎን፣ አድራሻዎን ወይም የፖለቲካ ፓርቲዎን የመለወጫ ቀነ-ገደቡ ቅዳሜ ኦገስት 22 ቀን ነው።*

## የመራጭ ምዝገባ

### ኦንላይን

**www.RegisterToVoteMA.com**

Registry of Motor Vehicles ID (የሞተር ተሽከርካሪዎች መዝገብ መታወቂያ) ከሌለዎት መመዝገቢያ ቅጽዎን አትመው 689 Massachusetts Avenue፣ STE 1፣ Cambridge፣ MA 02139-3302 ወደሚገኘው Election Commission Office (የምርጫ ኮሚሽን ጽሕፈት ቤት) በፖስታ መላክ ይኖርብዎታል

### በአካል

***Cambridge Election Commission፣ 689 Massachusetts Avenue፣ STE 1 በመደበኛ የሥራ ሰዓታት።***

እ.ኤ.አ ኦገስት 22 ቅዳሜ ቀን ላይ በየትኛውም አስቀድሞ ድምጽ መስጫ ቦታ ላይ ከ9 ኤ.ኤም እስከ 3 ፒ.ኤም ወይም በElection Commission office ከ9 ኤ.ኤም እስከ 5 ፒ.ኤም ድረስ መመዝገብ ይችላሉ።

# አስቀድሞ ድምጽ መስጠትን መረዳት

**አስቀድሞ ድምጽ መስጠት ምንድን ነው?**

አስቀስሞ ድምጽ መስጠት ከምርጫ ቀኑ በፊት ድምጽ መስጠት የሚቻልበት ዕድል ነው። በአካልም ሆነ በፖስታ ድምጽ መስጠት የሚችሉ ሲሆን፣ የድምጽ መስጫ ወረቀትዎም በምርጫ ቀኑ ገቢ ይደረግልዎታል። አስቀድሞ ድምጽ መስጫ ጊዜው በ Massachusetts ስቴት ሕግ መሠረት ተደንግጎ የተቀመጠ ነው።

**አስቀድሞ ድምጽ መስጠት የሚችለው ማን ነው?**

በCambridge ውስጥ ያለ ማንኛውም የተመዘገበ መራጭ አስቀድሞ ድምጽ መስጠት በሚቻልበት ጊዜ ውስጥ ድምጽ መስጠት ይችላል! በጣቢያው ሳይገኙ ድምጽ ከሚሰጥበት አሠራር (absentee voting) በተለየ መልኩ አስቀድመው ድምጽ ለመስጠት ሰበብ ወይም ምክንያት አያስፈልግዎትም!

**አስቀድሜ ድምጽ መስጠት የሚችለው የት ነው?**

በምርጫ ቀኑ ላይ ከሚተገበረው አሠራር በተለየ መልኩ የምርጫ ጣቢያ አይመደብልዎትም። ከታች ከተዘረዘሩት የCambridge አስቀድሞ ድምጽ መስጫ ቦታዎች ውስጥ ወደ የትኛውም መሄድ ይችላሉ። በ689 Massachusetts Avenue የሚገኘው የElection Commission office ለመጀመሪያ ዙር የስቴት ምርጫዎች አስቀድሞ ድምጽ መስጫ ጣቢያ ሆኖ አያገለግልም።

**አስቀድሜ ድምጽ መስጠት የምችለው መቼ ነው?**

አስቀድሞ ድምጽ መስጫ ጊዜው እ.ኤ.አ ከቅዳሜ ኦገስት 22 ቀን 2026 ዓ.ም ጀምሮ እስከ አርብ ኦገስት 28 ቀን 2026 ዓ.ም ድረስ ይቆያል።
አስቀድሞ ድምጽ መስጠት የሚቻልባቸው ሰዓታት ከቀን ቀን ሊለያዩ ስለሚችሉ ከዚህ በታች ያለውን መርሃ-ግብር ይመልከቱ።

**አስቀድሞ ድምጽ ከመስጠት ይልቅ በተመደበው የምርጫ ቀን ላይ ደምጽ መስጠት ብፈልግስ?**

አስቀድመው ድምጽ ካልሰጡ በምርጫ ቀን ወደተመደቡበት የድምጽ መስጫ ጣቢያ በመሄድ ድምጽ መስጠት ይችላሉ። **እርስዎ የተመደቡበት ድምጽ መስጫ ጣቢያ ተለውጦ ሊሆን እንደሚችል እባክዎን ልብ ይበሉ።**

የተመደቡበትን ምርጫ ጣቢያ የያዘ የመራጭ ማሳወቂያ ካርድ ከምርጫ ቀኑ በፊት የሚደርስዎ ሲሆን፣ እንደ አማራጭም www.cambridgema.gov/pollinglocationsን በመጎብኘት የተመደቡበትን ጣቢያ መመልከት ይችላሉ።

የምርጫ ጣቢያዎች እ.ኤ.አ ማክሰኞ ሴፕቴምበር 1 ቀን 2026 ዓ.ም ላይ ከ7 ኤ.ኤም እስከ 8 ፒ.ኤም ክፍት ይሆናሉ። ድምጽ መስጠት የሚችሉት አንድ ጊዜ ብቻ ነው፤ አስቀድመው ድምጽ ከሰጡ በምርጫ ቀኑ ላይ ድምጽ መስጠት አይችሉም።

## ቀደም ብሎ በአካል ድምጽ መስጠት የሚቻልባቸው ጊዜያት እና ቦታዎች

| | |
|---|---|
| **ቅዳሜ፣ ኦገስት 22 ቀን** | 9 ኤ.ኤም - 3 ፒ.ኤም |
| **እሑድ፣ ኦገስት 23 ቀን** | 9 ኤ.ኤም - 3 ፒ.ኤም |
| **ሰኞ፣ ኦገስት 24 ቀን** | 8:30 ኤ.ኤም - 8 ፒ.ኤም |
| **ማክሰኞ፣ ኦገስት 25 ቀን** | 8:30 ኤ.ኤም - 5 ፒ.ኤም |
| **ረቡዕ፣ ኦገስት 26 ቀን** | 8:30 ኤ.ኤም - 5 ፒ.ኤም |
| **ሐሙስ፣ ኦገስት 27 ቀን** | ከ8:30 ኤ.ኤም - 5 ፒ.ኤም |
| **አርብ፣ ኦገስት 28 ቀን** | ከ8:30 ኤ.ኤም - 12 ፒ.ኤም |

በ689 Massachusetts Avenue የሚገኘው የ**Election Commission office** ለመጀመሪያ ዙር የስቴት ምርጫዎች አስቀድሞ ድምጽ መስጫ ጣቢያ ሆኖ **አያገለግልም።**

መራጮች ከታች ከተዘረዘሩት አስቀድሞ ድምጽ መስጠት ከሚቻልባቸው የምርጫ ጣቢዎች ውስጥ ወደ አንዱ መሄድ ይኖርባቸዋል።


### አስቀድሞ ድምጽ መስጠት የሚቻልባቸው ጣቢያዎች

Valente **ቤተ መጻሕፍት**
826 Cambridge Street፣ Berkshire Street ላይ ባለው የጎን መግቢያ

Cambridge Water Department (የCambridge **የውኃ መምሪያ**)
250 Fresh Pond Parkway

Main library (**ዋና ቤተ መጻሕፍት**)
449 Broadway

# በፖስታ ቀደም ብሎ ድምጽ መስጠት




## 01

### ማመልከቻውን ያግኙት

ከwww.MailMyBallotMA.com መተግበሪያውን ያውርዱ ወይም የእርስዎን ስም፣ Cambridge ውስጥ የሚኖሩበትን አድራሻ፣ ድምጽ መስጫ ወረቀቱ እንዲላክ የሚፈልጉበትን አድራሻ እና ፊርማዎን የያዘ ጥያቄ በጽሑፍ ያቅርቡ። **ያልተመዘገቡ መራጮች የትኛውን የፓርቲ ድምጽ መስጫ ወረቀት እንደሚፈልጉም መግለጽ አለባቸው።**

በዲሞክራቲክ ወይም ሪፐብሊካን ፓርቲ ውስጥ ከተመዘገቡ ድምጽ መስጠት የሚችሉት በተመዘገቡበት ፓርቲ ድምጽ መስጫ ወረቀት ላይ ብቻ ነው። በተለምዶ ገለልተኛ ተብለው ከሚጠሩት ያልተመዘገቡ ግለሰቦች ውስጥ የሚካተቱ ከሆነ በመጀመሪያው ዙር ምርጫ ላይ ድምጽ መስጠት የሚፈልጉበትን የፓርቲ ድምጽ መስጫ ወረቀት መርጠው ገለልተኛ እንደሆኑ መቀጠል ይችላሉ

## 02

### ማመልከቻውን ይላኩ

ፊርማዎ ያረፈበትን ማመልከቻ በኢሜይል፣ በፋክስ ወይም በፖስታ ይላኩ።
ማመልከቻዎን የሚልኩት በኢሜይል ከሆነ ፊርማዎ በእጅዎ ከተጻፈ ፊርማ ጋር ሊነፃጸር በሚችል መንገድ ሊቀመጥበት ይገባል።
ኤሌክትሮኒክ ፊርማዎች፣ ስካን የተደረጉ ማመልከቻዎች እና የማመልከቻ ፎቶግራፎች ተቀባይነት አላቸው። በኮምፒውተር የተተየቡ ፊርማዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም።

ኢሜይል፦ **elections@cambridgema.gov**

ፋክስ፦ **617-349-4366**

ፖስታ፦ **689 Massachusetts Avenue, STE 1, Cambridge, Ma 02139-3302**

## 03

### የድምጽ መስጫ ወረቀትዎን ለመመለስ ያሉት አማራጮች፦

- ከድምጽ መስጫ ወረቀትዎ ጋር የቀረበውን ለፖስታ-የተከፈለበት ማሸጊያ በመጠቀም ድምጽ መስጫ ወረቀቱን በፖስታ ይመልሱ።
- በተደነገጉት አስቀድሞ ድምጽ የመስጫ ሰዓታት ውስጥ አስቀድሞ ድምጽ ወደሚሰጥበት ጣቢያ በመሄድ በፖስታ የታሸገውን ድምጽ መስጫ ወረቀት ለምርጫ ባለስልጣኑ መመለስ።
- የድምጽ መስጫ ወረቀትዎን በCambridge ከሚገኙት ስድስት (6) የድምጽ መስጫ ሳጥኖች ውስጥ በአንዱ ያስገቡ። በዚህ መመሪያ የመጨረሻ ገጽ ላይ ድምጽ መስጫ ሳጥኖች የሚገኙባቸው ቦታዎች በዝርዝር ተቀምጠዋል።

### አስፈላጊ ቀነ ገደቦች

**ድምጽ መስጫ ወረቀት መጠየቅ የሚቻልበት ቀነ ገደብ፦**
ኦገስት 25 ማክሰኞ ቀን 5 ፒ.ኤም።

ማመልከቻዎ በወቅቱ መላኩን ለማረጋገጥ የElection Commission በተቻለ ፍጥነት እንዲያመለክቱ ይመክራል።

**ድምጽ መስጫ ወረቀት መመለሻ ቀነ ገደብ፦**
ሴፕቴምበር 1 ቀን 2026 ዓ.ም 8 ፒ.ኤም።

### ድምጽ መስጫ ወረቀትዎን በኦንላይን ይከታተሉ

www.TrackMyBallotMA.com

### ጥያቄዎች አሉዎት?

CambridgeMA.gov/EarlyVoting ላይ ድር ጣቢያችንን ይጎብኙ

በ617-349-4361 ወደ Election Commission Office ይደውሉ

elections@cambridgema.gov ላይ ኢሜይል ይላኩልን

ማመልከቻዎን ለመጻፍ እገዛ ፈልገው ከElection Commission ጋር ለመግባባት ግን አስተርጓሚ ካስፈለገዎ፣ እባክዎ ወደ 617-865-2273 ይደውሉ። አስተርጓሚው ከከተማው አስተዳደር ተወካይ ጋር ያገናኝዎታል።